# እናት ሆይ! ጀርባሽን እሚዘነችሩትን እስከ መቼ እሹሩሩ ትያለሽ?

*August 17, 2016*

**በላይነህ አባተ *(abatebelai@yahoo.com)***

እናት ሆይ! የደራሲና የዘፋኝ መዋኛ ባህሩ፣ የድርሰትና የዘፈን መቅጃ ምንጩም ማህበረሰብና የማህበረሰቡ ባህል መሆኑን ልብሽ ይነግርሻል፡፡ ከማህበረሰቡ የባህል ባህር የወጣ ድርሰትና ዘፈን ከባህር እንደ ወጣ አሳ እድሜው አጭር መሆኑን ዛሬ ተነበው ነገ የማይደገሙት ድርሰቶች፣ ዛሬ ተደምጠው ነገ የማይደመጡት ዘፈኖች ያረጋግጡልሻል፡፡ የማህበረሰቡን ደስታ፣ ችግር፣ መከራና ሐዘን ያልዳሰሰ ድርሰትና ዘፈን ከባህር ውጪ እንደቆየ አሳ የሞተ መሆኑንም አእምሮሽ ያስረዳሻል፡፡ የማህበረሰቡ ችግር፣ መከራና እልቂት መንስኤ የሆኑትን ከንቱዎች እሚያወድስ ድርሰትና ዘፈን እንዲያውም እንደ ጠነባ አሳ ወዲያው እንደሚወረወር ህሊናሽ ያሳውቅሻል፡፡

እናት ሆይ! ጣሊያን ገረድ ሊያደርግሽ ሲደነፋ ቀረርቶና ፉከራዎች በዋሽንት፣ በክራር፣ በመሰንቆ፣ በበገና፣ በጸናጽል፣ በከበሮና በሌሎችም ባህላዊ መሳሪያዎች ታጅበው እንደታደጉሽ ታስታውሻለሽ፡፡ በእነዚህ ባህላዊ መሳሪያዎች የታጀቡ ቀረርቶዎችና ፉከራዎች ስንት ድንበር ጠባቂ ጀግኖች እንዳፈሩልሽ ትዝ ይልሻል፡፡ እነዚህ የጀግና መኮትኮቻ ቀረርቶዎችና ፉከራዎች በምድርሽ እንዳይሸለሉ ከሃያ አምስት አመታት በፊት በድንበር ሻጮች እንደተከለከሉም ትገነዘቢያለሽ፡፡ ድንበር ሻጮችን በመከተልም ብዙዎቹ የኪነ-ጥበብ ልጆችሽ ከቀራርቶና ከፉከራ እንደራቁ ታውቂያለሽ፡፡ አንዳንዶች ራሳቸውን የጠሉ ዘፋኞችም ቀረርቶና ፉከራን እንደ ስልጣኔ-አልባ ሕዝብ ኪነ-ጥበቦች በመቁጠር ከራሳቸው የባህል ባህር ወጥተው ከማያውቁት የባህል ባህር ገብተው እንደ ጀማሪ ዋናተኛ ሲንጨቧረቁና የባህል ተገዥ ባሪያዎች ሲሆኑም ትታዘቢያለሽ፡፡

ያለሸበት የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ዘመን ከቱርኩ፣ ከደርቡሹና ከጣሊያኑ የወረራ ዘመን የከፋ መሆኑን የተቆረጠው አንገትሽ፣ የተሸጠው ፍሪንባሽ፣ የተሰነጣጠቀው ሆድ እቃሽና የወደቀው ክብርሽ እንደሚያስረዳ ታውቂያለሽ፡፡ የዛሬው መከራሽ ካለፉት መከፋቱን በባሩድ የተረሸኑት፣ ከገደል የተወረወሩት፣ በወህኒ የተሰቃዩት፣ በርሃብ የተጨረገዱት፣ በስደት ባህር የገቡት፣ በሊቢያ የተቀሉት፣ ባረብ ታንቀው የሞቱት፣ ባፍሪካ በእሳት የጋዩትና በእስር የተንገላቱት ልጆችሽ ምስክሮች እንደሆኑ ትረጃለሽ፡፡ ታዲያ ለዚህ ከድሮው የከፋ ህመምሽ ስንት ምሁራን መድኃኒት ፍለጋ ኳተኑልሽ? ስንት አቀንቃኞች ሰቆቃሽን አቀነቀኑልሽ? በሌጣ እግርሽ ተጉዘሽ ኩበት ለቅመሽና በኩበት ጪስ ታጥነሽ እንንቻ አነጉተሽ ያስተማርሻቸው ምሁራን ሲመረቁ የገቡትን መሐላ ዘንችረው ለምን እጀ አመድ አፋሽ አደረጉሽ? በቅኔሽና በዜማሽ እንጀራ እሚጎርሱት ካህናትና ዘፋኞችሽ ይሉኝታን ጎርድመው ለምን ፊታቸውን አዞሩብሽ?

የቆሎ ተማሪሽ ቁራሽ ሲለምንና እንደ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ በኮር አባልነት የበረዶ ስኳር(ዓይስ ክሬም) መላስ ሳይጀምር "ያሁኑ ይባስ!" ይል እንደነበር ታስታውሻለሽ፡፡ ያሁኑ ብሶ አንዳንድ ምሁራንና ዘፋኞችሽ ካንቺ ከእናታቸው ፊታቸውን ከማዞርም አልፈው የጣሊያንን ያልተሳካ ምኞት ከሚፈጥሙት ጡት ነካሽ ልጆችሽ ጋር ቦጫጭቀውና በከረጢት ቋጥረው መቃብር ሊወስዱሽ ተሰልፈው ትመለከቻለሽ፡፡ እንዲያውም ይንጠስልሽ ብለው ልቅሶሽን ሰርግ ለማስመሰል ስለ ልማት ሲወሽክቱና ስለ ህዳሴ ሲዘፉኑ ትሰሚያለሽ፡፡ አንገትሽን ገዝግዘው የቀነጠሱትን፣ ጀርባሽን ተልትለው የሸጡትን፣ ሆድ እቃሽን ወጋግተው ወንፊት

ያደረጉትና የልጆችሽን ደም እንደ ዓባይ ፏፏቴ ያፈሰሱትን “አምሳለ ሙሴ” ብለው እየደረሱና እየዘፈኑ ካንቺ አልፈው ከታሪክ፣ ከፍትህና ከእግዚአብሔር ሲጣሉም ታዳምጫለሽ፡፡ ታዲያ ካንቺ፣ ከታሪክ፣ ከፍትህና ከእግዚአብሔር ለተጣሉት ምሁሮችሽና ዘፋኞችስ ምን ምክር አለሽ? ጣልያን ገረድ ሊያደርግ ሲወርሽ መንገድ እያሳዩ ፋኖዎችሽን ካስፈጁትና ለፋኖዎችሽ ገዳዮች እንቁላል አቅራቢ ከነበሩት እርጉም ልጆችሽ ምን ተማርሽ?

እናት ሆይ! እናት ሆደ ሰፊን እያወጋሽ እስከ መቼ ባንዳን ትታገሻለሽ? እናት አትጨክንምን እየተረትሽ ጡት ነካሽ ልጆችሽን እስከ መቼ ጡት አጉርሰሽ ታድሪያለሽ፡፡ የወለደ አይጥልምን እየተረትሽ ጀርባሽን እሚዘነችሩትን እስከ መቼ እሹሩሩ ትያለሽ?

ነሐሴ ሁለት ሺ ስምንት ዓ.ም.